



# «እነሱማ ባይኖሩ»!

## (ለኦሎምፒክ ጀግኖቻችን)

ለኢትዮጵያዊነት እስትንፋስ - ሊቋረጥ ለሚያቃትተው፣
ለሰንደቅ ዓላማዋ ክብር - በጠላቶቿ ለተናቀው፣
ለሕዝቧ ህልውና መሰረት - በመከራ ለታጀለው፣
ለሉዓላዊነት ታሪኳ - አደጋ ላንዣበበው...
*እነሱማ ባይኖሩ!*
ለስትንፋሷ ነፍስ እሚዘሩ፣
ባንዲራዋን እሚያስከብሩ፣
ኅብረ-ዜማ እሚያስዘምሩ፣
ላገር ታሪክ እሚሠሩ...
ምን ይውጣት ነበር ኢትዮጵያ..?
በጨለማው ዘመን ብርሃን እሚሆኗት
የደበዘዘ ሥሟን በወርቅ እሚጽፉላት
እነሱማ ባይኖሯት!!
**ወርቅ አበቦች ልጆቿ!!**
**የስፖርት ዓለም ጀግኖቿ!!**

የእማማ ኢትዮጵያ አበሳ - ሆኖብን የሕመም ቋት፣
ቀቢፀ-ተስፋ ተሞልተን - እህህ... ስናቃስት፣
የሰረፀብን ያገር ፍቅር - በርትቶብን «ልክፍቱ»፣
አቅመ-ቢሶች ሆንንና - እያንገላታን ቁጭቱ፣
እጃችንን ዘርግተን - ከመጸለይ በቀር፣
መላ ውሉ ጠፍቶብን - ጨልሞብን ስንቸገር፣
ያገር ጥቃት ቁጭትን - በድል እሚበቀሉ፣
ሕመማችንን እሚያጥቡልን - በፈዋሽ የዕንባ ጸበሉ፣
*እነሱማ ባይኖሩ!*
እንደ ርግብ እየበረሩ፣
የድል ተስፋን እሚያበስሩ፣
አገር ሕዝብን እሚያኮሩ፣
ሥማችንን እሚያስጠሩ፣
እንዴትስ እንሆን ነበር እኛ..?
በሥነ-ልቦና ሕመም - ነጋ-ጠባ ስንሰቃይ
እነሱማ ባይኖሩን - ያገር አድባር ያለም ሲሳይ!
**ክቡር ዕንቁ አንበሶቹ!!**
**የኦሎምፒክ ጀግኖቹ!!**

ሥመ-ጦቢያ ተቀብራ - ባንዲራዋ ተረምርማ፣
ያገር አድባር ተመንግሎ - ስንኳትን በጨለማ፣
ካመት-ዓመት ብቅ እያሉ - ተስፋ እንዳትሞት እሚነግሩ፣
አንገት ላንገት ተቃቅፈው - የኅብረት ዘዴን ሊያስተምሩ፣
ባረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀዩ - እጅግ ደምቀው እያበሩ፣
«የሾኽ አክሊል» እየደፉ - ባለም መድረክ እየዞሩ፣
መከራችን እንዲያከትም - የድል ብሥራት እሚያበስሩ...
እንዴት፣ እንዴት ይኮን ነበር? *እነሱማ ባይኖሩ!!*
**ውብ አበቦች ደማቆቹ!!**
**የኦሎምፒክ ጀግኖቹ!!**

ጌታቸው አበራ

ነሐሴ ፩ ሺህ ዓ/ም
(ኦገስት 2008)



